ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ
Forum for Social Studies (FSS)

ተኅሳስ 2003 ዓ.ም. *የፖሊሲ ፍሬ ሀሳቦች* ቁጥር 25

# አረቂ የማምረት፣ ንግድና ፍጆታ ማኅበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ በኢትዮጵያ

*የማኅበራዊ ጥናት መድረክ በሀገሪቱ የልማት ችግሮች ዙሪያ ፖሊሲ-ነክ ምርምሮችን የሚያደርግ ለትርፍ ያልተቋቋመና መንግስታዊ ያልሆነ አገር በቀል ድርጅት ነው፡፡*

*የምርምር ውጤቶቹን ለፖሊሲ አውጪዎችና ጉዳዩ ለሚመለከታቸው አካላት እንዲደርሱ ያደርጋል፣ ሕዝባዊ ውይይቶችን ያዘጋጃል፣ የተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎችን ጋብዞ ያወያያል፡፡*

*በአዲስ አበባ (በ97.1 ሞገድ) እና በአዋሳ (በ100.9 ሞገድ) ከተሞች ኤፍ.ኤም.ራዲዮ ጣቢያዎች ልማት ነክ ጉዳዮችን እያዘጋጀ ያሰራጫል፡፡*

*በድረ-ገጹ የሕትመት ውጤቶቹን ዝርዝር ያቀርባል፡፡*

*በርዕሱ ዙሪያ ሐሳብ መሰንዘር የምትፈልጉ በኢሜይል አድራሻችን ላኩልን፡፡*

የኢትዮጵያን የወደፊት የልማት እርምጃ የሚፈታተኑ መሰናክሎች በርካታ ናቸው፡፡ ከተፈጥሯዊ እስከ ሥርአታዊ፣ ለረጅም ጊዜ ከቆየው የፖለቲካ አለመረጋጋት እስከ የዘመናችን እጅግ ፈጣን የህዝብ ብዛት መጨመር፣ ሲጠራቀም ከመጣው የኢኮኖሚ ኋላቀርነት እስከ የቅርቡ የኤች.አይ.ቪ/ ኤድስ ወረረሽኝና ሌሎች ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ተደማምረው የሀገሪቱን ዘርፈ-ብዙ እድገት በማንተት ላይ ይገኛሉ፡፡ ከነዚህ በተጨማሪ በቅርቡ ብቅ ብቅ እያሉ የመጡ የተለያዩ አሉታዊ ህብረተሰባዊ ክስተቶች ተጨማሪ ጫና እያሳደሩ ናቸው፡፡ ከእነዚህም ውስጥ በአጠቃላይ የጎጂ ሱሶች፣ በተለይም የአረቂ/ካቲካላና የጫት ተጠቃሚነትና ሱሰኝነት፣ እንዲሁም የወሲባዊ መዳሪያ ዎችና (ፖርኖግራፊ) የቁማር ቤቶች አዘውታሪነት እና የመሳሰሉት በዋነኛነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ እነዚህ የኋለኞቹ ደግሞ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እየተስፋፉ የመጡ በመሆናቸው አሳሳቢነታቸውን ያህል ተገቢው የጥናት ትኩረት አልተቸራቸውም፡፡

እነዚህ በከፍተኛ ፍጥነት በመዛመት ያሉት አሉታዊ ሕብረተሰባዊ ክስተቶች ውሱን የሆነውን የሃገሪቱን ጥሪት ከመሻማት አልፎ ገና በወጉ ባልተዳረሱት የጤናና የደህንነት ጥበቃ በመሳሰሉት ማኅበራዊ አገልግሎቶች ላይ ያለውን ጫና ይበልጥ የሚያከብዱ በመሆናቸው ባህርያቸውን፣ መንስዔያቸውን፣ ፋይዳቸውንና መፍትሔያቸውን በጥልቅ ማጥናት ስኬታማ የልማት ዕቅድ ለመንደፍ ይረዳል፡፡

## መነሻ

የዚህ ጥናት ርዕስ የሆነው የአበሻ አረቂ ሙስሊሞች በዋናነት ከሚኖሩባቸው አካባቢዎች በስተቀር በየቦታው የሚገኝ፣ የብዙ ኢትዮጵያውያን በተለይ የገጠር ነዋሪዎች ተመራጭ የሆነ መጠጥ ነው፡፡ የአመራረቱ፣ የስርጭቱና የፍጆታው ክንዋኔዎችም በአንድነት የህብረተሰቡ ድርና ማግ ሆነው ከሚቆጠሩበት ደረጃ ደርሰዋል፡፡ በመሆኑም፣ የአረቂን አመራረት፣ አሻሻጥና አጠጣጥ በተሟላ መልኩ ማጥናት ባሕርያቱን ለመለየት፣ ጥቅምና ጉዳታቸውን ለመረዳትና መፍትሔ ጠቋሚ የፖሊሲ ሀሳቦችን ለማመንጨት ያለውን ጠቀሜታ በማሰብ ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ በዚህ ጉዳይ ላይ ካለፈው ዓመት ጀምሮ ጥናት ሲያካሂድ ቆይቷል፡፡ የጥናቱን ውጤትም ሕዝባዊ የውይይት መድረክ በማዘጋጀት ለባለድርሻ አካላት ከማቅረቡም በላይ በሕትመትም ለሕዝብ አሰራጭቷል፡፡ የጥናቱ ዋና ዋና ግኝቶችም በዚህ የፖሊሲ ፍሬ ሀሳቦች እትም እንደሚከተለው ተጨምቀው ቀርበዋል፡፡

## አላማና የመረጃ አሰባሰብ ስልት

የጥናቱ አላማ፣ ምን ያህል የአበሻ አረቂ በምን ያህል ህዝብ በመላ ሃገሪቷ ይመረት፣ ይሸጥና ይጠጣ እንደሆነ የመለካት ጉዳይ ሳይሆን፣ ከምን፣ በየት፣ በማን፣ እንዴት፣ እንደሚመረት፣ እንደሚሸጥና እንደሚጠጣ፤ ማንን በተመለከተ፣ ምን አይነትና በምን ደረጃ ጥቅምና ጉዳት እንደሚያስከትል መረጃ ማቅረብና የመፍትሄ ሀሳቦችን መጠቆም ነው፡፡ ስለዚህም ጥናቱ የተካሄደው የሀገሪቷን ህዝብ ወካይ በሆነ ናሙና ላይ በመመስረት አይደለም፡፡ የመስክ ጥናቱ ሆን ተብሎ የተካሄደው በአረቂ ምርታቸው፣ ሽያጫቸው፣ ወይም ፍጆታቸው ታዋቂ በሆኑ አምስት ቦታዎች ነው፡፡ እነሱም በሱሉልታ ወረዳ፣ በደብረብርሃን ከተማና በአጎራባችዋ የባሶና-ወራና ወረዳ፣ በደምበጫ ወረዳ፣ በቸሃ ወረዳ እና በአርሲ ነገሌ ከተማ በሚገኙ ስፍራዎች ናቸው፡፡

በተጨማሪም አጠቃላይ የመስክ ጥናቱ እጅግ በርካታ ሰዎችን ያካተተ

የዳሰሳ ጥናት ስልት የተከተለ በመሆን ፋንታ፤ ውስን ግን በቂ ከሆኑ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ሰዎች ጥልቅ ግንዛቤ የሚሰጥ መረጃ በመሰብሰብ ላይ ያተኮረ ነበር። የመስክ ጥናቱ በነዚህ በተመረጡ ቦታዎች በሚካሄድበት ጊዜ ለናሙና ከተመረጡ አረቄ አውጪዎችና ሻጮች፣ የማህበረሰብ መሪዎች፣ የልማት ሰራተኞች፣ የአረቄ አውጪ-ሻጮች ልጆች፣ ባል፣ የረዥም ርቀትና የአካባቢ የአረቄ የጅምላ ነጋዴዎች፣ ሸማቾች፣ ቀማሽ-ደላሎች፣ የጤና ባለሙያዎች፣ የፖሊስ መኮንኖችና የወረዳና የቀበሌ አስተዳደር ተወካዮች፤ በጠቅላላው 73 ከሚሆኑ የአካባቢው ሰዎች ጋር በተደረጉ የቡድንና የተናጠል ውይይቶችና ጥልቅ ቃለ መጠይቆች አማካኝነት ጠቃሚ መረጃ ተሰብስቧል። ይህንን የመጀመሪያ ደረጃ መረጃ በፅሁፍ ከሚገኙ ተጨማሪ መረጃዎች ጋር በማጠናቀርና በመተንተን ጥናቱ ላነሳቸው የምርምር ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት ተሞክሯል። የመስክ ጥናቱ በመስከረምና በጥቅምት 2002 ዓ.ም. የተካሄደ ሲሆን፤ በህዳርና በነሀሴ ወራት ደግሞ ተጨማሪ መረጃዎች በአዲስ አበባ ከሚገኙ ባለሙያዎች ተሰብስበዋል።

## ዋና ዋና ግኝቶች

***የአረቄ ወደ ሀገር ውስጥ መግባትና መስፋፋት፡-*** በአሁኑ ጊዜ የአባሻ አረቄ ወይም ካቲካላ ከአንዳንድ የሙስሊም ማህበረሰብ ብቸኛ አካባቢዎች በስተቀር በተለያየ ደረጃ በሀገሪቷ ተዳርሷል። ይሁንና አረቄ የማውጣትና የመጠጣት ክስተት ወደሀገሪቷ መግባትና መለመድ የጀመረው ከ19ኛው ክፍለ ዘመን ሁለተኛ አጋማሽ ወዲህ እንደሆነ የፅሁፍ ማስረጃዎች ይጠቁማሉ። አረቄ በትናንሽ ከተሞችና በገጠሩ የተዛመተውና የተዳረሳው ደግሞ ከ1950ቹ ወዲህ ሲሆን፣ ዋነኛ እመርታዎቹን ያደረገው ደግሞ መጀመሪያ ከ1967 የመሬት ይዞታ መሻሻል ማግሥትና በመቀጠል ደግሞ ከ1983 የመንግስት ለውጥ ጋር ተያይዞ የመጣውን የግብርና ምርቶች ዋጋ ከፍ እንዲልና ወደ ገበሬው እጅ የሚገባውን ጥሬ ገንዘብ ያሳደገው የነፃ ገበያ ለውጥ ተከትሎ እንደሆነ ጥናቱ ከተደረገባቸው አካባቢዎች የተገኙ መረጃዎች ይጠቁማሉ። ከሕብረተሰባዊ ለውጥ ዘገምተኛነት ጋር በተነፃፃሪነት ሲታይ ይህ እጅግ ፈጣን የሆነ ግስጋሴ እንደ መሆኑ ሁሉ፤ የአረቄ አወጣጥ፣ አሻሻጥና አጠጣጥ ዘይቤ በነባሩ ባህል እምብዛም ሳይገራ ተስፋፍቷል።

***አመራረት፡-*** አረቄን ለማምረት የተለያዩ ግብአቶች የሚያስፈልጉ ሲሆን፤ ዋና ዋናዎቹም እህሎች፣ ብቅል፣ ጌሾና ውሃ ናቸው። ለምርቱ የሚውሉት የእህል አይነቶች ከቦታ ቦታ የሚለያዩ ቢሆንም በዋናነት ግን በቆሎ፤ ማሽላና ስንዴ በብዛት በስራ ላይ ይውላሉ። አልፎ አልፎም እንክርዳድ ለአረቄ ምርት በግብአትነት እንደሚውል ጥናቱ አረጋግጧል። የአረቄ አመራረት በሁለት ዋና ሂደቶች ውስጥ ያልፋል። የመጀመሪያው ማፍላት (fermentation) ሲሆን፤ ይህም መጠንሰስና መደፍደፍ የተባሉትን ስራዎች ያካትታል። ይህ ሂደት ጠላን ከመጥመቅ ጋር በእጅጉ ተመሳሳይ ሲሆን፤ ጥናቱ በተካሄደባቸው ቦታዎች ድፍድፉን ለመደፍደፍ የእህል ዱቄት በቂጣ፣ደረቆት፣ ወይንም እንኩሮ መልክ ተዘጋጅቶ በስራ ላይ ይውላል። ሁለተኛው፤ በተለምዶ ማውጣት (distillation) የሚባለው ሲሆን የአረቄውን ድፍድፍ በእንስራ ጥዶ ከአንድ ሰዓት እስከ ሁለት ሰዓት ለሚሆን ጊዜ በመቀቀል አረቄው የሚወጣበት ሂደት ነው።

***የማምረቱና የአመራረቱ ፋይዳዎችና ጠንቆች፡-*** አረቄ የማውጣት ስራ ከሞላ ጎደል በሴቶች የተያዘ ነው። ዘርፉ ለብዙ የገጠርና የከተማ ሴቶች መተዳደሪያ መሆኑን ጥናቱ አረጋግጧል። በተለይም፤ በተለያዩ ምክንያቶች ሌላ መተዳደሪያ ለሌላቸው የገጠር እማወራዎች ትንሽ የመነሻ ገንዘብ በቻ የሚጠይቀው የአረቄ ማውጣት ስራ ዋነኛ፤ አንዳንዴም ብቸኛ መተዳደሪያ ነው። ሳገቡ የገጠርና የከተማ ሴቶችም ቢሆን፤ የአረቄ ማውጣት ስራ የራሴ የሚሉት ገቢ እንዲኖራቸው የሚያስችል መሆኑን ለማረጋገጥ ተችሏል። በተጨማሪም ከአረቄ ምርት የሚገኝ ገቢ ለቤተሰብ ብሎም ለአካባቢው ማህበረሰብ ጉልህ አስተዋፅኦ እንዳለው ጥናቱ ያረጋገጠ ሲሆን፤ ይህም የሚጎላው በተለይ መጠጡ በስፋት በሚመረትባቸው የከተማ አካባቢዎች (ለምሳሌ አርሲ ነገሌ) ነው።

ምንም እንኳን አረቄ ማምረት ዘርፈ-ብዙ ጥቅም ያለው ቢሆንም፣ የዚያኑ ያህል ጉዳቶችም አሉት። የአረቄ ማምረት ስራ ከግብአት ዝግጅት ጀምሮ እስከ አረቄ ማውጣት ድረስ ማገዶ መጠቀም የሚጠይቅ በመሆኑና አሰራሩም ማገዶ የማይቆጥብና ኋላ-ቀር በመሆኑ በእፅዋት ሽፋን ላይ ብሎም በአካባቢ ተፈጥሮ ሀብት ላይ የሚያስከትለው ጉዳት ከፍተኛ ሆኖ ተገኝቷል። ከዚህም በተጨማሪ በገጠራማ የጥናቱ አካባቢዎች በስፋት የታየው ኩበትን ለአረቄ ማገዶ የመጠቀም ሁኔታ በመሬት ለምነት ላይ ያለው ተፅእኖ ቀላል አይደለም። ሌላው አሉታዊ ተፅእኖ ከምግብ ዋስትና ጋር የተያያዘ ሲሆን፤ ለዚህም ምክንያቱ እጅግ ሰፊ መሬት በየአመቱ ለአረቄ ምርት ለሚውለው ብዙ ሺህ ኩንታል እህልና ጌሾ ማምረቻነት መዋሉ ነው። በመጨረሻ የሚነሳው አሉታዊ ተፅእኖ በአረቄ አውጭ ሴቶችና በልጆች ላይ የሚደርሰው የጤና ችግር ነው። በተፋፈጉ ማዕድ ቤቶችና ታዛዎች በኋላ-ቀር ዘዴ አረቄ የሚያወጡት ሴቶች በዚሁ የተነሳ በተለያዩ የመተንፈሻ አካላትና ሌሎች በሽታዎች የሚጠቁ ሲሆን፤ ልጆችም ለተመሳሳይ በሽታዎችና አልፎ አልፎም አሰቃቂ አደጋዎች (ለምሳሌ በእሳት የመቃጠል፣ትኩስ የአረቄ አተላ ውስጥ የመውደቅ አደጋ) ይጋለጣሉ።

***ጅምላ ንግድ፡-*** የአረቄ ጅምላ ንግድ ከተሞችን ከሌሎች ከተሞችና ከየአካባቢያቸው የገጠር ማኅበረሰቦች ጋር አቆራኝቶ የሚሄድ ሰፊ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ነው። አንዳንድ ከተሞችና አንዳንድ አጎራባቾቻቸው ጭምር ከፍተኛ መጠን ያለው አረቄ የሚመረትባቸው በመሆናቸው ዋነኛ የጅምላ አረቄ ንግድ መነሻዎች

ናቸው፡፡ አርሲ ነገሌ፣ ደብረ ብርሃንና ደምበጫ በዚሁ ቅደም ተከተል ለዚህ አይነት ንግድ ተጠቃሾች ሲሆኑ፤ ከአርሲ ነገሌ ብቻ በመኪና ተጭኖ በየአቅጣጫው የሚጓዘው አረቄ በአመት ከ32 ሚሊዮን ሊትር በላይ መሆኑ የጅምላ ንግዱን ክፍተኛነት በበቂ ሁኔታ ያሳያል፡፡ በዘርፉ ከተሰማሩት ዜጎች ውስጥ አረቄ በብዛት በሚመረትባቸው አካባቢዎች ከሚገኙ ገበያዎች አረቄ አሰባስበው ሲያበቁ ወደ ፍጆታ አካባቢ ገበያዎች አጓጉዘው በዚያ ለቸርቻሪዎች የሚያቀብሉ ነጋዴዎች ዋነኞቹ ናቸው፡፡ የውሎ-ገባው የአረቄ ጅምላ ንግድ በአመዛኙ በሴቶች የሚካሄድ ሲሆን፤ መንገድ ላይ አዳርን የሚያስከትለውን እንደ አርሲ ነገሌ-አዲስ አበባ-ዱበር ያለውን የረጅም ርቀት ንግድ ግን ወንድ የጅምላ ነጋዴዎች ይቆጣጠሩታል፡፡

***ችርቻሮ ንግድ፡-*** ከላይ ከተጠቀሱት የጅምላ ነጋዴዎች ላይ እንደየአቅማቸው በአነስተኛ እቃ ተረክበው በተራቸው በገጠር ሆነ በከተማ በሚገኙ የንግድ ወይም የመኖሪያ ቤቶቻቸው ለተቀማጭ መሸተኛ በመለኪያ የሚኮምሩና ለይዞ-ሂያጅ ደግም በጠርሙስ የሚሸጡ ከቸርቻሪዎች መካከል አንደኛው አይነት ሲሆኑ፤ የራሳቸውን አረቄ አውጥተው የሚቸረችሩና ከአውጪዎች በቀጥታ ገዝተው የሚቸረችሩቱ ደግሞ ሁለተኛው አይነቶች ናቸው፡፡ እንደ አረቄ ማውጣቱ ሁሉ፣ የአረቄ ችርቻሮም ከሞላ ጎደል በሴቶች የተያዘ ዘርፍ ነው፡፡ አረቄ የሚቸረቸርባቸው ስፍራዎችም መሸታ ቤቶች ብቻ ሳይሆኑ መኖሪያ ቤቶችም ጭምር ናቸው፡፡ እንዲያውም በዋነኝነት በንግድ ቤትነት ያገለግሉ እንደሆነ እንጂ፤ ሙሉ በሙሉ ለአረቄ መነገጃነት ብቻ የሚያገለግሉቱ ከሌሉ የሚቆጠሩ ናቸው፡፡ በተጨማሪ፣ የአረቄ ንግድ ከሌሎች ምግቦችና መጠጦች ጋር በተጓዳኝነት የሚቸረቸሩባቸው የንግድ ቤቶችም በከተሞች ውስጥ ይገኛሉ፡፡ የአረቄ ቤቶች በተለያዩ ደረጃዎች የሚገኙ ሆነው፣ እንደየአካባቢው አቅም በተለያዩ የኑሮ ደረጃ ላይ ያሉ ሰዎች እንደ ገንዘብ አቅማቸውና ፍላጎታቸው የሚያዘወትሯቸውም በየከተሞቹ ይገኛሉ፡፡ በገጠሩ ግን ይህ ነው የሚባል የሀብት ልዩነት ባለመኖሩ የተነሳ ይህ አይታይም፡፡ የአረቄ ችርቻሮና የዝሙት ስራ ተዳዳሪነት ተያያዥነት አላቸው፤ በተለይ በከተሞች፡፡

እንደ አመራረቱ ሁሉ፤ የአረቄ ችርቻሮም ይህ ነው የሚባል ስርአት የያዘ አይደለም፡፡ የአረቄ ቤቶቹን የመክፈቻና የመዝጊያ ሰዓት፣ የጠጭዎቹን ሆነ የቀጂዎቹን እድሜና ፆታ፣ አብሮ የሚቀርብን ማጣጫ፣ ወዘተ… የሚወስኑ ምንም አይነት ነባር ደንቦች የሉትም፡፡

***ፍጆታና አጠጣጥ፡-*** ጥናቱ በተካሄደባቸው አካባቢዎች በሙሉ፣ የአረቄ ፍጆታ ከፍተኛ መሆኑንና እየጨመረ በመሄድ ላይ እንደሚገኝ ጥናቱ አረጋግጧል፡፡ ከየአካባቢው ሽማግሌዎች የተገኘው ግምታዊ መረጃ እንደሚያሳየው ከሆነ፣ እድሜው ለአቅመ-አዳም ከደረሰው ህዝብ (በተለይም ከወንዱ) ውስጥ አብዛኛው አረቄ አዘውታሪና ወደ አንድ-አስረኛ የሚጠጋው ደግሞ የመጠጡ ቁራኛ ሲሆን የየግለሰብ ጠጭው አማካይ የፍጆታ መጠንም ከፍተኛና እየጨመረ በመሄድ ላይ የሚገኝ ነው፡፡ የአረቄ ፍጆታ መጠን ከአካባቢ አካባቢ ከመለያየቱ ባሻገር፣ አረቄ ከሴቶች ይልቅ በወንዶች፣ ከወጣቶች ይልቅ በጎልማሶችና በአረጋውያን፣ እናም ለጥሬ ገንዘብ ተዳራሽነት ባላቸው ሰዎች ይበልጥ እንደሚጠጣ ታውቋል፡፡

እንደ አሻሻጡ ሁሉ፣ የአረቄ አጠጣጥም በአመዛኙ ቅጥ-የለሽ ነው፡፡ በአሁኑ ዘመን፣ አረቄ የማይጠጣበት ቦታ፣ ወቅትና፣ ማኅበራዊ አጋጣሚ ፈልጎ ማግኘት ያስቸግራል፡፡ በቤተክርስቲያን ደጀ-ሰላሞች፤ በጥምቀተ-ባሕሮች፣ በገበያ አካባቢዎች፣ በንግድ ቤቶችና፣ በመኖሪያ ቤቶች ሁሉ አረቄ ይቀርባል፡፡ አልፎ አልፎ በጠዋት ይታለፍ እንደሁ እንጅ፣ ቀን ከሌሊት ይጠጣል፡፡ በሰርግ፣ በተዝካር፣ በማሕበርና በመሳሰሉት ድግሶች ላይ ብቻ ሳይሆን እንደ ጅጌ ወይም ደቦ፣ እዝን፣ የፍንጥር፣ የደስደስና እርቅ በመሳሰሉ አጋጣሚዎች ሁሉ ታዳሚው ከቁጥጥር ውጭ እስከሚሆን ድረስ አረቄ ይጠጣል፡፡ አረቄ ከአቅርቦት ባሻገር የሚጠጣውን መጠን በሚገቱም ሆነ ጉዝጓዝ በመሆን ሰውነት የመጉዳት ኃይሉን የሚያለዝብ ምግብ መቀደሙን በሚደነግጉ ማንኛውም ዓይነት ማኅበራዊ ወጎች እንደማይገዛ ታውቋል፡፡

***የአረቄ መጠጥ የሚያስከትለው ጉዳት፡-*** ከጥናቱ ግኝቶች መካከል አሳሳቢዎቹ በአረቄ መጠጣት ምክንያት የሚከሰቱ ቀጥተኛና ተዘዋዋሪ ጉዳቶች ናቸው፡፡ ወንጀሎችና ጠብ ብዙውን ጊዜ የአረቄ ስካርን ተከትለው የሚከሰቱ ሲሆኑ አረቄ መሸጫ ቤቶችም የወንጀል እቅድ ማውጫ እንዲሁም የአምባጓሮ መነሻ ቦታዎች ሆነው ተገኝተዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም፣ የአረቄ ሱሰኛ የሆኑ ባሎች በሚስቶቻቸውና በልጆቻቸው ላይ የሚያደርሱዋቸው የቃላትና አካላዊ ጥቃቶች በቤተሰብ አባላት ላይ ከሚያስከትሉት መንፈሳዊና አካላዊ ጉዳቶች በተጨማሪ ለቤተሰብ ሰላም መደፍረስ ብሎም መፍረስ ምክንያት ሆነው ተገኝተዋል፡፡ አረቄን ማዘውተር የጠጪዎቹን አካላዊና አዕምሯዊ ጤና እንደሚጎዳ ከማህበረሰብ አባላትና ከጤና ባለሙያዎች የተገኙ መረጃዎች አመልክተዋል፡፡ ከዚህም በተያያዘ ጠጪዎቹ በአረቄ ከሰከሩ በኋላ ከትዳር ጎደኞቻቸው ውጭ ጥንቃቄ የጎደለው የግብረስጋ ግንኙነት የሚፈፅሙ ሲሆን፣ የኤች. አይ. ቪ.ን መኖርም እስከመካድ ይደርሳሉ፡፡ አረቄ ባለው ከፍተኛ የአልኮል መጠንና የማስከር ችሎታ የተነሳ ጠጪዎቹ አካላቸውን መቆጣጠር እየተሳናቸውና የማመዛዘን ችሎታቸውን እያጡ ለተለያዩ አደጋዎች ይጋለጣሉ፡፡ በአረቄ የሰከሩ እንዲሁም የመጠጡ ቁራኛ የሆኑ ታካሚዎችም የህክምና አገልግሎት በሚቀበሉበት ወቅት በእጅጉ የሚያስቸግሩ ሲሆን፣ የህክምና ባለሙያን ምክርም

አይተገብሩም፡፡ እነሱን በማስተናገድም የጤና አገልግሎት ተቋማቱ የህዝብ ሀብትና ጊዜ ያባክናሉ፡፡ አረቄ አመራረቱም ሆነ አሻሻጡ ንፅህና የሚጎድለው ሲሆን አንዳንድ ባዕድ አካላትም (ለምሳሌ እንዶድ፣ የምድር እምቧይ) ይጨመሩበታል፡፡ ይህ ሁኔታ በጤና ላይ ጉዳት ሊያስከትል የሚችል መሆኑ ጥርጥር የለውም፡፡ በተጨማሪም አረቄ መጠጣት የቤተሰብን የገንዘብ አቅም በማመንመኑ፣ የምግብና የዘር እህሎች እንዲሁም የቤት እቃዎች ተሸጠው ገንዘቡ ለመጠጡ በመዋሉ፣ ጠጪዎቹ የስራ ፍላጎትና አቅም በማጣታቸውና በልማት ስራዎች ላይ ባለመሳተፋቸው የመጠጡ ቀጥተኛ ኢኮኖሚያዊ ጉዳት ከፍተኛ ሆኗል፡፡

ቀጥተኛ ያልሆኑት አረቄ የመጠጣት ጉዳቶችን በተመለከተ፤ ከአረቄ ጋር በተያያዘ በሚከሰቱ ጠቦችና አምባጓሮዎች የተነሳ የሚባክኑት የጠበኞቹና የአስታራቂዎቻቸው የስራ ሰዓታት፣ በነኝህ ግጭቶች ምክንያት የሚጎዱ ሰዎችን በማሳከምና በማከም የሚወጣው ጊዜና ጉልበት፣ እንዲሁም ፀጥታን ለማስከበርና ህግ ተጥሶ ሲገኝም ፍትህ ለመስጠት የሚሰማራው የሰው ሀይልና ተያያዥ ወጭዎች ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ በጠቅላላው፣ ሌሎች ጥናቶች እንደሚያመልክቱት፣ የአልኮል መጠጦች በአንድ ሀገር ላይ የሚያደርሱት ኢኮኖሚያዊ ጉዳት መጠን የሀገሩን ጠቅላላ የውስጥ ምርት 3 ከመቶ የሚያክል መሆኑ የአረቄ መጠጥን መዘዝ በተዘዋዋሪ ይጠቁማል፡፡

## ማጠቃለያና ከፖሊሲና ቁጥጥር ጋር ተያያዥ የሆኑ የመፍትሄ ሀሳቦች

የጥናቱ አጭር ድምዳሜ የአረቄ ምርት፣ ንግድና መጠጥ በሀገሪቱ ላይ እያደረሱት ያለው አጠቃላይ ጉዳት አይነተ-ብዙና የመዘዙም መጠን ከፍተኛ እንደሆነ ነው፡፡ በአንፃሩ ደግሞ ምርትና ንግዱ በበኩላቸው ከሚያስከትሏቸው ጉዳቶች ባሻገር የማይናቁ ኢኮኖሚያዊ ፋይዳዎችም እንዳሏቸውና ከነዚህም ዋነኛው እጅግ በርካታ ለሆኑ ዜጎች በተለይ ደግሞ ባል-አልባ ለሆኑና መነሻ የገንዘብ ጥሪትም ሆነ አማራጭ ሙያ ለሌላቸው እማወራዎች መተዳደሪያ ማስገኘታቸው ነው፡፡ በዚህም የተነሳ አረቄን በተመለከተ እርምጃ መውሰዱ የግድ ሆኖ ሳለ፣ መወሰድ ያለባቸውና የሚችሉትም እርምጃዎች ይህንን እንቆቅልሽ ታሳቢ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡

እስከዛሬ ድረስ የአረቄን ችግር ለመፍታት በቤተ ክርስቲያኖች፣ በዕድሮችና በእርዳታ ሰጪ ድርጅቶች ቀስቃሽነት በአካባቢ ደረጃ አልፎ አልፎ የተሞከሩ እርምጃዎች እንደነበሩና እነዚህም የአረቄን መረን የለቀቀ አጠጣጥ በመግታት ላይ ብቻ ያነጣጠሩ መሆናቸውን ጥናቱ አሳይቷል፡፡ ይህ የሚጠቁመው ደግሞ፣ የአረቄ መጠጥን ጎጂ ጎኖች ብቻ በመመልከት የአረቄ ምርትና ንግድን በጠቅላላ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ በሕግ ከልክሎ ለማሰናበት መሞከር እንደማይገባና እንደማይቻል ነው፡፡

በተጨማሪም ጥናቱ፣ ከአለፈው ከ2002 ዓ.ም. ጥር ወር ጀምሮ የአልኮል መጠጥ፣ ንግድና ፍጆታ ቁጥጥር ይደረግባቸውና መልክ ይይዙ ዘንድ እየተመቻቹ የመጡትን አገራዊና ዓለም-አቀፋዊ የፖሊሲ አቅጣጫዎችና መዋቅሮች በተገቢው ዘግቧል፡፡ በመሆኑም ያቀረባቸው የመፍትሄ ሀሳቦች እነዚህን ሥርዓታዊ ማዕቀፎች ከግምት ውስጥ ያስገባል፡፡ ጥናቱ፣ ቀደም ብለው የተጠቀሱትን አጠቃላይና ዝርዝር ግኝቶቹን መሰረት ያደረጉ፣ የሀገሪቱን ነባራዊ ሁኔታም ያገናዘቡና ሊተገበሩ የሚችሉ ዝርዝር የመፍትሄ ሀሳቦችን ይጠቁማል፡፡ እነዚህ በድምሩ ሃያ አምስት የሆኑ የመፍትሄ ሀሳቦች በሦስት አጠቃላይ አርእስት ስር ተዘርዝረው ቀርበዋል፡፡ አርእስቱም የሚከተሉት ናቸው:-

(ሀ) የግለሰቡን ባሕርይ በመለወጥ ላይ የሚያተኩሩ እርምጃዎች፣

(ለ) በግለሰቦች ዙሪያ ያሉትን አካባቢዎች፣ ማለትም ምርቱን ወይንም አረቄውን ራሱን፣ አቅራቢውን ወይንም ሻጩን፣ እና አቀራረቡን ወይም አሻሻጡን መልክ የሚያሲዙ የደንብ እርምጃዎች፣ እና

(ሐ) የነዚህና የሌሎች ተጨማሪ የአረቄ ቁጥጥር ደንቦችን አዘገጃጀትና አተገባበር የሚመለከቱ አሠራሮች፡፡


**የራስወርቅ አድማሴ (ዶ/ር)**

**ኢዛና አምደወርቅ (አቶ)**



**ምንጭ**:- Yeraswork Admassie and Ezana Amdework. 2010. *The Aräqe Dilemma: The Socioeconomics of Traditional Distilled Alcohol Production, Marketing, and Consumption in Ethiopia*. FSS Monograph No. 6. Addis Ababa: Forum for Social Studies (FSS).



ምስጋናና ማሳሰቢያ

ይህ ሰነድ የታተመው በሊጋሾች ቡድን የገንዘብ ድጋፍ ነው፡፡ ለሰነዱ ይዘት ሙሉ ኃላፊነቱ የደራሲያኑ ሲሆን በምንም ሁኔታ የለጋሾች ቡድንን ወይም የአሳታሚውን አቋም እንደሚያንፀባርቅ ተደርጐ መወሰድ የለበትም፡፡



**አድራሻ:- ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ፣ ፖ.ሳ.ቁ 25864 ኮድ 1000 አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ**

❄ **ስልክ 011-629 78 88/91** ❄ **ፋክስ 011-629 78 89**

❄ **ኢሜይል: fss@ethionet.et** ❄ **ድረ-ገፅ www.fssethiopia.org.et**